Washington State Health Care Authority

# ጉርምስና እድሜ ላይ ያሉ የፀባይ ጤና አያያዝ አማራጮች

የታካሚ ስም                                                                 የህክምና ማህደር ቁጥር

እድሜያቸው ከ13 እስከ 17 አመት የሆኑ ጎረምሳዎች የአዕምሮ ጤና ግምገማ ወይም የአደንዛዥ እጽ ችግር ህክምና የሚፈልጉ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች በህጋዊነት ስለሚገኙ ሁሉም የህክምና አማራጮች ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ እነዚህም በጎረምሳ የተጀመረ ሕክምና (ቀደም ሲል በትንሽ-የተጀመረው ሕክምና) ፣ በቤተሰብ የተጀመረው ሕክምና (ቀደም ሲል በወላጅ የተጀመረው ሕክምና) እና ያለፈቃደኛነት የሚደረግ ህክምናን ያጠቃልላል፡፡ ከጁላይ 2019 ጀምሮ ፣ HB 1874 በ RCW 71.34 ስር የሚገኘውን በቤተሰብ የተጀመረው ሕክምና (FIT) ቋንቋ በማስፋት ያለጎረምሳው ፈቃድ ለወላጅ ፣ ለአሳዳጊ ወይም የባህሪ የጤና አገልግሎት ሰጪ ሊገለጽ የሚችል መረጃን በተመለከተ የውጪ ታካሚዎች ሕክምና አገልግሎቶችን እና መመሪያዎችን ለማካተት በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ የባህሪይ ጤና (BH) ሕክምና ተደራሽነት ያስፋፋል፡፡

## በጎረምሳ የተጀመረ ሕክምና (RCW 71.34.500-530)

እድሜው ከ13 እስከ 17 አመት የሆነ ጎረምሳ ልጅ ያለወላጅ ፈቃድ በተመላላሽ ታካሚነት ወይም በውስጥ ታካሚነት የአዕምሮ ጤና ግምገማ ወይም የአደንዛዥ እጽ ችግር ህክምና ግምገማ መጠየቅ ይችላል፡፡ ተቋሙ በተመላላሽ የአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ እጽ ችግር ህክምና አስፈላጊነት ላይ ከተስማማ, ጎረምሳው አገልግሎቶች ሊሰጠው ይችላል፡፡ የውስጥ ታካሚ የሚፈቀደው የተቋሙ ሀላፊ ባለሙያ ሰው የውስጥ ታካሚነት ህክምናው አስፈላጊነት ላይ ከተስማማ ብቻ ነው፡፡ ከ13 አመት በታች ለሆነ ልጅ የውስጥ ታካሚነት ህክምና ለማድረግ የወላጅ ስምምነት ወይም ከጸደቀ አሳዳጊ የተገኘ ስምምነት ያስፈልጋል፡፡

## በቤተሰብ የተጀመረው ሕክምና (RCW 71.34.600-670)

ወላጅ ፣ አሳዳጊ ፣ የእንጀራ ወላጅ ፣ ተንከባካቢ ዘመድ ፣ ሌላ ዘመድ ወይም ስልጣን የተሰጠው ግለሰብ ከ13 እስከ 17 አመት የሆነው ጎረምሳ ልጅን ወደ ማንኛውንም የአእምሮ ጤንነት ግምገማ እና ህክምና ተቋም ፣ ሆስፒታል ፣ የሕመምተኛ ተቋም ወይም የተፈቀደለት የአደንዛዥ እጽ ችግር (SUD) ሕክምና ፕሮግራም በመውሰድ እና በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ የአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር እንዳለበት እና የውስጥ ወይም የተመላላሽ ሕክምና የሚያስፈልገው መሆኑን ለማወቅ በአእምሮ ጤና ግምገማ ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር ግምገማ እንዲደረግለት ይጠይቁ። ግምገማው በውስጥ የታካሚነት ድባብ/አቀማመጥ ውስጥ ከ72 ሰአታት በላይ ሊወስድ አይችልም፡፡ ለተመላላሽ ታካሚ ወይም ለውስጥ የአእምሮ ጤንነት ታካሚ ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር ግምገማ የጎረመወሳው ልጅ ስምምነት አያስፈልግም፡፡ እባክዎን የወላጅን አዲስ ትርጉም ይመልከቱ ***RCW 71.34.020(25)(a)***።

***እባክዎን የሚከተለው ያስተውሉ፡*** *በ FIT ደንብ መሠረት ለጎረምሳ ህክምና ለመስጠት ማንም አገልግሎት ሰጪ ግዴታ የለበትም። ሆኖም በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኝ አንድ ልጅ ለህክምናው ፈቃደኛ አለመሆኑ ተቋሙ አገልግሎቶችን ላለመስጠት ብቸኛ የውሳኔ መሠረት አይሆንም።*

## በቤተሰብ የተጀመረ የተመላላሽ እና ጽኑ የተመላላሽ ሕክምና

ዕድሜው ከ 13 እስከ 17 ዓመት የሆነው ጎረምሳ ልጅ የአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር እንዳለበት እና የተመላላሽ ሕክምና እንደሚያስፈልገው በባለሙያ ከተወሰነ አገልግሎቱ ለታዳጊው በ FIT በኩል ሊሰጥ ይችላል። FIT አንድ ወላጅ በ 3 ወር ጊዜ ውስጥ ለአንድ ጎልማሳ ከአንድ ልዩ ባለሙያ ጋር በሚደረግ 12 የተመላላሽ የአዕምሮ ጤንነት እና / ወይም የ SUD ክፍለ-ጊዜዎችን ማወቅ እና መስማማት እንደሚችል ይገልጻል። አገልግሎት የሚሰጠው የተመላላሽ ባለሞያ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኝ አንድ ወጣት በቤተሰብ ተነሳሽነት ሕክምና ስር የተመላላሽ ሕክምና ማግኘቱን በመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት ውስጥ እንዲሁም በ 3 ወር ጊዜ ውስጥ በየ45 ቀኑ በጤና እንክብካቤ ባለሥልጣን (HCA) ሀላፊነት በተሰጠው ገምጋሚ ማሳወቅ አለበት፡፡ የሕክምናውን ጊዜ ተከትሎ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኝ ልጅ ከአንድ አገልግሎት ሰጪ ጋር ለተጨማሪ ሕክምና ፈቃድ መስጠት አለበት።

## በቤተሰብ የተጀመረው የውስጥ ታካሚ ሕክምና

ዕድሜው 13 እስከ 17 ዓመት የሆነው ጎረምሳ የአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር እንዳለበት እና የውስጥ ታካሚ ህክምና እንደሚያስፈልገው በባለሙያ ሰው ከተወሰነ ወላጁ ወይም አሳዳጊው በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ ለህክምና እንዲቆይ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የውስጥ ህክምና መርሃ ግብር ወጣቱ ለህክምና መቀመጥ አለበት ብሎ የሚያምን ከሆነ የውስጥ ህክምና ተቋም ግምገማው በተጠናቀቀ በ 24 ሰዓታት ውስጥ በጉርምስና

ዕድሜ ላይ የሚገኝ ልጅ ለህክምና እንደተቀበለ በ HCA ሀላፊነት ለተሰጠው ገምጋሚ ማሳወቅ አለበት፡፡ የውስጥ ህክምና መርሃግብር በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ ከ 7 ቀናት በላይ መቀመጥ አለበት ብሎ የሚያምን ከሆነ ፣ የውስጥ ህክምና መርሃ ግብር ለቀጣይ የውስጥ ሕመምተኛ ህክምና ፍላጎት ግምገማ መጠናቀቅ እንዳለበት ለ HCA ማሳወቅ አለበት፡፡ ከግምገማው ከአምስት ቀናት በኋላ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ ከህክምና ቦታው ለመውጣት ለከፍተኛ ፍርድቤት ይግባኝ የማለት መብቱ በህክምና ቦታው መነገር አለበት። በዚህ ምእራፍ ስር ህክምና የሚያገኝ ማንኛውም በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ ወደህክምና የገባው በፈቃደኝነት ካልሆነ ወይም የባለሙያ ሰው ወይም የተመደበለ የችግር መላሽ (DCR) በዚህ ክፍል ስር ያለፈቃደኛነት የሚደረግ የህክምና ሂደቶች እስካላስጀመረ ድረስ በ HCA ሀላፊነት የተሰጠው ገምጋሚ ግምገማ በሰጠ በ 30 ቀናት ውስጥ ከህክምና ተቋም መውጣት አለበት፡፡

በ HCA ሀላፊነት የተሰጠው ገምጋሚ ግምገማ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ወጣት ለውስጥ-ታካሚ ሕክምና የሕክምና መመዘኛ የማያሟላ መሆኑን ከወሰነ ወላጁ ወይም አሳዳጊው ወዲያውኑ ማወቅ እና ወጣቱ በ 24 ሰዓታት ውስጥ መለቀቅ አለበት፡፡ በዚህ ሁኔታ ፣ ወላጁ ወይም አሳዳጊው እና የህክምና ቦታው ሁለቱም በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ በውስጥ ህክምና ውስጥ መቆየት በሕክምና አስፈላጊ ነው ብለው ካመኑ ተቋሙ ከ HCA ግምገማው ቀጥሎ ባለው ሁለተኛው የፍርድ ቀን ድረስ ወጣቱን ያቆያል፡፡ ይህ በ**RCW 13.32A.191** መሰረት ወላጅ ወይም አሳዳጊ አደጋ ላይ ያለ ወጣት ማመልከቻ እንዲያስገባ ጊዜ ይሰጣል፡፡ የቤተሰብ እርቅ አገልግሎቶች (**RCW 13.32A.040**) በልጆች፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ (DCYF) በኩል ይሰጣሉ፡፡

በቤተሰብ ተነሳሽነት ሕክምና መሠረት ወደ የውስጥ ሕክምና ተቋም የገባ ወጣት ወላጆች በጽሑፍ የመልቀቂያ ጥያቄ በሰጡበት ጊዜ ወዲያውኑ ከጽሕፈት ቤቱ መውጣት አለባቸው፡፡

## ያለፈቃደኛነት የሚደረግ ህክምና (RCW 71.34.700-795)

የ 13 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ጎረምሳ በእራሳቸው ወይም በሌሎች ማለትም ጽኑ አካል ጉዳት ባለው ላይ ከባድ ጉዳት የመፍጠር አዝማሚያ ካለው እና በአፋጣኝ የአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም የውስጥ ህክምና የሚያስፈልገው እና በፈቃደኝነት ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆነ ያለፈቃደኛነት የሚደረግ ህክምና ለመስጠት በ DCR ለመገምገም ጎረምሳው እስከ 12 ሰዓታት ድረስ ሊያዝ ይችላል። የፍቃደኝነት ወይም ያነሰ ገዳቢ የሕክምና አማራጮች ከሌሉ እና በአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ እጽ ችግር ምክንያት ወጣቱ ከባድ ጉዳት የመፍጠር አዝማሚያ ወይም ጽኑ አካል ጉዳት እንዳለው DCR ከወሰነ ወጣቱ ተቋም ውስጥ ሊቆይ ይችላል፡፡ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኝ ልጅ የአደንዛዥ እጽ ችግር ያለፈቃደኛነት የሚደረግ ህክምና የሚሰጠው ደህንነቱ የተጠበቀ የመውጫ አያያዝ እና የማረጋጊያ ተቋም ወይም ተቀባይነት ያለው የአደንዛዥ እጽ ችግር ህክምና መርሃግብር የሚገኝ ከሆነ እና ለወጣቱ በቂ ቦታ ካለ ብቻ ነው።

በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ ቀደም ሲል የውስጥ የአእምሮ ጤንነት ወይም የአደንዛዥ እጽ ችግር ህክምና ተቋም ተቀባይነት ካገኘ ያለፈቃደኛነት የሚደረግ ህክምና የፍርድ ሂደቶችን ለመቀጠል በአእምሮ ጤና ወይም የአደንዛዥ እጽ ችግር ህክምና ባለሞያ እና በሠራተኞቹ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ያለፈቃደኛነት የሚደረግ ህክምና ህግ መሰረት ወጣቱ ቅዳሜና እሁድን እና በዓላትን ሳያካትት በመጀመሪያ ለህክምናው እስከ 72 ሰዓታት ድረስ ሊቆይ ይችላል፡ ፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ተቋሙ ተጨማሪ ህክምና አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ወጣቱ ለተጨማሪ 14 ቀናት እንዲቆይ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡ በ 14 ቀናት ማብቂያ ላይ ተቋሙ ለተጨማሪ የውስጥ-ሕክምና እስከ 180 ቀናት ድረስ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

DCR ወጣቱን ካልያዘ ወላጁ ወይም አሳዳጊው ለፍርድ ቤት ማመልከቻ በማስገባት እና የ DCR ሪፖርትን እና / ወይም ማስታወሻዎችን በመስጠት በ 71.05.201 መሠረት ውሳኔው እንዲመረመር ሊፈልግ ይችላል፡፡

በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ልጅ በሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ወይም በአነስተኛ ገደብ አማራጭ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከሆስፒታል ከተለቀቀ እና የተለቀቀበትን ሁኔታ ወይም የፍርድ ቤት ማዘዣ ሁኔታዎችን የማይከተል ከሆነ ፣ ወይም በእንቅስቃሴያቸው ላይ ከፍተኛ መባባስ ከታየ ወጣቱ በ DCR መገምገም እና በቁጥጥር ስር መሆን ይችላል እንዲሁም ለአእምሮ ህመም ህክምና ወደ የውስጥ ግምገማ እና ህክምና ተቋም ወይም ወደ ጤናማ የመልቀቂያ አያያዝ እና ማረጋጊያ ተቋም ወይም ተቀባይነት ላለው የአደንዛዥ እጽ ችግር ሕክምና መርሃግብር መዛወር ይችላል፣ ተቋሙ የሚገኝ ከሆነ እና ለወጣቱ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር ህክምና በቂ ቦታ ካለው። ለተጨማሪ ድጋፍ ወይም ጥያቄዎች የአካባቢያዊ የባህሪ ጤና ቀውስ መስመር ይደውሉ፡፡

**የአቅራቢዎች የግዴታ ግምገማዎች ማስታወቂያ**

FIT ከተቀበለ በ 24 ሰዓታት ውስጥ አቅራቢው በ HCA ሀላፊነት የተሰጠውን ገምጋሚ፣ የ FIT አስተዳደር ጽ / ቤት ደህንነቱ በተጠበቀ ኢሜይል በ fitreporting@fitadministration.com ወይም ደህንነቱ በተጠበቀ ፋክስ በ 206-859-6432 ማሳወቅ አለበት።

ማስታወቂያው የሚከተሉትን ያካትታል፡

- ስም እና የትውልድ ቀን
- የ FIT የመግቢያ ቀን ወይም የ FIT ለውጥ
- በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለው ወጣት የሚኖርበት አውራጃ ፣ እና
- የመድን አይነት

ወጣቱ በገባ ከ 7 እስከ 14 ቀናት መካከል ፣ እና ተመላላሽ ህክምና ወይም ጽኑ ተመላላሽ ህክምና ሲቀጥል በየ45 ቀኑ አገልግሎት ሰጪው የሕክምና አስፈላጊነት እንዲገመገም የሚከተሉትን መረጃዎች በ HCA ሀላፊነት ለተሰጠው ገምጋሚ መላክ አለበት:

- የመቀበያ መረጃ ወረቀት
- የመቀበያ ግምገማ ማስታወሻ
- የመልቀቂያ ማጠቃለያ

☐ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ላሉት ወጣቶች ስለሚኖሩት የሕክምና አማራጮች በፅሁፍ እና በቃላት ማስታወቂያ ተሰጥቶኛል፡፡

| **የወላጅ / አሳዳጊ ፊርማ** | **ቀን** | **የመገልገያ ተወካዩ ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|---|---|
| ______________________ | ______ | ______________________ | ______ |

☐ **የወላጅ / ሞግዚት ፊርማ ወይም ፈቃድ ማግኘት አልተቻለም።**

**ያልተፈረመበት ምክንያት፡**

| **የተቋሙ ተወካይ ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|
| ______________________ | ______ |

**በቤተሰብ ስለተጀመረው ሕክምና ለበለጠ መረጃ ፣ እባክዎን የሚከተለውን ያነጋግሩ-**
HCAFamilyInitiatedTreatment@hca.wa.gov

## ወቅታዊ መረጃ

ማርች 17/ 2020፡

- የመግቢያ እና የግምገማ አድራሻ ወደሚከተለው ተቀይሯል:
  **FIT አስተዳደር ጽሕፈት ቤት** በ fitreporting@fitadministration.com ላይ ደህንነቱ በተጠበቀ ኢሜይል ወይም በ 206-859-6432 በአስተማማኝ ፋክስ በኩል።